**ሆመቾ ሆስፒታል ደርሶ መልስ ትራንስፖርት፥ በገጠር ቀበሌያት ሆስፒታል ለመሄድ ትራንስፖርት አጥተዉ የሚቸገሩትን መርዳት**

የሥራ ፕሮፖዛሉ የቀረበዉ:
ለሀዲያ ዞን ማህበራዊ ጉዳይ: ሆሳዕና

ቀን:

የሥራ ፕሮፖዛሉን ያቀረበዉ:
በፓ/ር ገ/ ወልድ አባተ
አስተባባሪ
የአባተ መኒሶ ቤተ ሰብ ማህበር በጎ አድራጎት
ሆመቾ ከተማ ግቤ ወረዳ ሀዲያ ዞን ደቡብ ኢትዮፕያ
ስልክ ቁጥር:

## ሆሙቾ ሆስፒታል ደርሶ መልስ ትራንስፖርት፥ በገጠር ቀበሌያት ሆስፒታል ለመሄድ ትራንስፖርት አጥተዉ የሚቸገሩትን መርዳት

### የፕሮጀክቱ ዋና ሀሳብ

የፕሮጀክቱ ዋና ሀሳብ የትራንስፖርት መኪና በማይገኝበት ገጤ ቀበሌት በትራንፖርት እጦት ለሚቸገሩ ሕመምተኞች ከቀበሌ ጤና ጣቢያ ወደ ሆሙቾ ሆስፒታል በማመላለስ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ነዉ።

### የፕሮጀክቱ አስፈላጊነት

በትራንስፖርት እጥረት ምክንያት የታመሙ ሰዎች ካልባሰባቸዉ ሀኪም ቤት መሄድ አይታሰብም። መተንፈስ እስከሚያቅታቸዉ ህመሙ ሲበረታ የአካባቢን ህዝብ በጡሩምባ መጥራት ይጀመራል። የሚሸከሙ ሰዎች ተጠርተዉ እስከሚሰበሰቡ ህምምተኛዉ የበለጠ ከተጎዳ በኋላ በቃሬዛ በቅርብ ወደሚገኘዉ ጤና ጣቢያ ይወሰዳል ህምምተኛዉ በድል በሆስፒታሉ የሚኖር ካልሆነ በስተቀር። ጤና ጣቢያ ለቀላል ህመም የሚያገለግል ስለሆነ በጠና ህመም የሄደዉ ህመምተኛ የሚያገኘዉ ዕርዳታ የመነመነ ነዉ። በቃሬዛ ወደ ቤታቸዉ ከተመለሱ በኋላ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። ሰዎች በዚህ አደጋ ሳይወድቁ መፍትሄ መፈለግ እጅግ አስፈላጊ ነዉ።

### የፕሮግራሙ ዝርዝር

በመደበኛዉ አሰራር መኪነዉ በሆሙቾ ሆስፒታልና በያንዳንዱ ቀበሌ ጤና ጣቢያ በቀን ሁለት ጊዜ አመላለሳል፣ አንዱ ከሰዓት በፊት ሁለተኛዉ ከሰዓት በኋላ። ይህም ወደ ሆስፒታል የመጡለመመለስ እንዲቻል ነዉ። ህይ ፕሮግራም ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ሊዛባ ይችላል። የትራንስፖርት አገልግሎት ሂሳብ የሚጠየቀዉ ከአገልግሎቱ በኋላ ይሆናል፣ የአገልግሎቱ ሂሳብ የሚሰላዉ አገልግሎቱን ለመቀጠል በሚያስችለዉ መጠን ይሆናል። ህመምተኛዉ ለአገልግሎቱ መክፈል እንደመይችል ሲረጋገጥ ሂሳቡ እስከ ዚሮ ድረስም ይወርዳል። የፕሮጀክቱ አላማ በዘለቄታነት ግቡን እንዲመታ እራሱን ችሎ ወደ መንቀሳቀስ በሚያስችል መልኩ ይንቀሳቀሳል። በመጀመሪያ ዓመት የስራ ማስኬጃ በጀት በአብዛኛዉ በርዳታ የሚሸፈን ሆኖ፣ በ 4ኛ ዓመት ወጪዉ በአብዛኛዉ ህብረተ ሰቡ በአባልነት በሚያዋጡት መዋጮ የሚሸፈን ይሆናል። አባል ያልሆኑ ህመምተኞች በአቅማቸዉ መጠን ለአገልግሎቱ የሚሰጡትና በባዶ ቦታ እግረ መንገዱን ከሚሳፈሩ ተራፈሪዎች የሚሰበሰብ ገንዘብ ይህ አገልግሎት እንዲቀጥል የሚያግዝ ይሆናል። የሚሰበሰበዉ ገንዘብ በሙሉ በህጋዊ ደረሰኝ ሆኖ በሂሳብ ባለሙያ ሂሳቡ ተሰርቶ ሪፖርት ለቦርዱና ለሚመለከታቸዉ ይቀርባል።

.

### ግቡና ዓላማዉ

ዓላማዉና ግቡ ትራንስፖርት በማጣት ሀኪም ጋ መምጣት ያልቻሉ ወይም በቃሬዛ የሚመጡ እንዳኖሩ ማድረግ ነዉ።

**ሆመቾ ሆስፒታል ደርሶ መልስ ትራንስፖርት፥ በገጠር ቀበሌያት ሆስፒታል ለመሄድ ትራንስፖርት አጥተዉ የሚቸገሩትን መርዳት**

**የጊዜ ገደብ**

| የሚሰሩ ስራዎች | ጊዜ |
|---|---|
| የአመ ቤተ ሰብ ማህበር በጎ አድራጎት መመስረቻ ማመልከቻ ይገባል | ጥር 29, 2015 |
| ማህበሩ ዕዉቅና ያገኛል | ሚያዝያ, 2015 |
| ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለዕርዳታ ድርጅት ይሰጣል | ግንቦት, 2015 |
| ከርዳታ ድርጅት የዕርታ ማስታወቂያ ይነገራል | ሰኔ, 2015 |
| መኪናና የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ገቢ ይሆናል | ጥር, 2016 |
| ሠራተኞች ይቀጠራሉ፣ በታቸዉን ይይዛሉ | የካቲት, 2016 |
| ከቀበሌ ተወካዮች ጋር በፕሮጀክቱ ሥራ አካሄድ ሰምምነት ይደረጋል | መጋቢት, 2016 |
| የትራንስፖርት አገልግሎት ይጀመራል | ሚያዝያ, 2016 |
| የሥራ ግምገማ ይደረጋል | ሰኔ, 2017 |
| አስፈላጊ ማሻሻያ ተደርጎ ሥራ ይቀጥላል | ሀምሌ, 2017 |
| የአባልነት ቅስቀሳ በየቀበሌዉ ይጀመራል | ነሃሴ, 2017 |
| የአባልነት ምዝገባና ገንዘብ መቀበል ይጀመራል | ጥቅምት, 2018 |
| የሥራ ግምገማ ይደረጋል | ሰኔ, 2018 |
| አስፈላጊ ማሻሻያ ተደርጎ ሥራ ይቀጥላል | ሀምሌ, 2018 |
| የሥራ ግምገማ ይደረጋል | ሰኔ, 2019 |
| ፕሮጀክቱ በዘላቂ ድርጅትነት ይዋቀራል | ሰኔ, 2019 |

**ሆመቾ ሆስፒታል ደርሶ መልስ ትራንስፖርት፥ በገጠር ቀበሌያት ሆስፒታል ለመሄድ ትራንስፖርት አጥተዉ የሚቸገሩትን መርዳት**

**በጀት**

| የሥራ ማንቀሳቀሻ በጀት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ገቢ** | 1ኛ ዓመት | 2ኛ ዓመት | 3ኛ ዓመት | 4ኛ ዓመት |
| ከአባተ ቤተ ሰብ በጎ አድራጎት አሜሪካ | 200,000 | 44,000 | 20,000 | 0 |
| አባተ መኒሶ ቤተ ሰብ ማህበር በጎ አድራጊት | 60,000 | 36,000 | 0 | 0 |
| ከበሽተኞች ክፈያ | 120,000 | 60,000 | 60,000 | 60,000 |
| ከተሳፋሪ ክፈያ | 120,000 | 120,000 | 180,000 | 240,000 |
| የተጠቃሚዎች አባልነት መዋጮ | 0 | 300,000 | 360,000 | 400,000 |
| የገቢ ድምር | **500,000** | **560,000** | **620,000** | **700,000** |
| **ወጪ** | | | | |
| የሾፌር ደመወዝ | 120,000 | 120,000 | 140,000 | 140,000 |
| ነዳጅ | 120,000 | 120,000 | 130,000 | 130,000 |
| የመኪና ሰርቪስና ጥገና | 40,000 | 40,000 | 40,000 | 45,000 |
| የአስተዳደር ወጪ (ሠራተኞች የቢሮ ዕቃ ቁሳቁስ የቢሮ ኪራይ ወዘተ) | 120,000 | 120,000 | 130,000 | 140,000 |
| ኮምፒዩተርና ፕሪንተር | 60,000 | 0 | 0 | 0 |
| ጥቃቅን ወጪዎች | 40,000 | 40,000 | 40,000 | 45,000 |
| **የወጪ ድምር** | **500000** | **440,000** | **480,000** | **500,000** |
| ከወጪ ቀሪ | 0 | 120,000 | 140,000 | 200,000 |
| የፈሰስ ገቢ ትርፍ | 0 | 20000 | 30,000 | 40,000 |
| **የመኪና ግዥ ተቀማጭ** | **0** | **140,000** | **170,000** | **240,000** |

**ሆመቾ ሆስፒታል ደርሶ መልስ ትራንስፖርት፥ በገጠር ቀበሌያት ሆስፒታል ለመሄድ ትራንስፖርት አጥተዉ የሚቸገሩትን መርዳት**

**የፕሮጀክቱ ግምገማ**

ፕሮጀክቱ በሶስት መንገድ ይገመገማል። አንደኛዉ ትራንፖርት አጥቶ በቃሬዛ ወደ ሀኪም ቤት የሚወሰድ ሰዉ በመኖር ወይም ባለመኖር፣ ሁለተኛዉ አገልግሎቱን ያገኙ ህመምተኞችና ሌሎች የሚመለከታቸዉ በሚሰጡት የዕርካታ ደረጃ አስተያየት ሲሆን፣ ሶስተኛዉ መገምገሚያ በመንግስት ዕዉቅና ባገኙ ኦዲተሮች የሚቀርብ የኦዲት ሪፖርት ነዉ።

**ሠራተኞችና የአደረጃጀት መረጃ**

ፓር ገ ወልድ አባተ፣ የአባተ መኒሶ ማህበር በጎ አድራጎት ቦርድ ሊቀ መንበርና ሥራ አስኪያጅ፥ ፕሮጀክቱን የሚመሩና፣ እንደ አስፈላጊነቱ የመንዳት አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን፣የትምህርት ደረጃቸዉ ከአድቬንቲስት ኮሌጅ በቲዎሎጂ የተመረቁና በቅስና የቤተ ክርስቲኖች መሪ በመሆን ከ30 አመት በላይ ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በግል የመንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

አብርሃም አባተ፣ የአባተ መኒሶ ማህበር በጎ አድራጎት የቦርድ አባልና ግምጃቤት፥ መኪና በመንዳትና ሌሎችን በማሰልጠን እንዲሁም ደግሞ የማህበሩን ንብረትና ጥሬ ገንዘብ በስርዓቱ ስራ ላይ እንዲዉል ሀላፊነት የሚወስዱ ሲሆን፣ የትምህርት ደረጃ 2ኛ ደረጃ፣ 5ኛ የመንጃ ፈቃድ፣ የከባድ መኪና በመንዳት ከ25 አመት በላይ የሰሩና አሁንም እየሰሩ የሚገኙ የንብረት ሀላፊነት መሸከም የሚችሉ ናቸዉ።

በየነ አባተ፣ የአባተ መኒሶ ማህበር በጎ አድራጎት የቦርድ ፀኃፊ፥ የቦርዱን ቃለ ጉባዔ የሚይዙ፣ ማህበሩ ድጋፍ እንዲያገኝ ከርዳታ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት የቢፈጥሩ ሲሆን፣ የትምህርት ደረጃ አስደዳደር ማስተርስ ዲግሪ ከአንድሪዩስ ዩኒቨርሲቲ አሜሪካ፣ በአካዉንቲንግ የመጀመሪያ ዲግሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በነርስንግ የመጀመሪያ ዲግሪ ከሚድ አሜሪካን ናዝሪን ዩኒቨርሲቲ አሜሪካ ያገኙ ሲሆን፥ በደብረ ብሪሃን ብርድልብስ ፋብሪካ፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በቀይ መስቀል፣በኢትዮጵያና ዉጭ አገር ዕርዳታ ድርጅት በሂሳብ ስራና ኦዲተርነት ካገለገሉ በኋላ በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ በነርስነት እያገለገሉ ይገኛሉ።

ትዕግስቱ አባተ፣የአባተ መኒሶ ማህበር በጎ አድራጎት ቦርድ አባልና አማካሪ በማህበሩ ጉዳዮች ላይ የዉሳኔ ድምፅ በመስጠትና በምክር አጋልግሎት የሚተባበሩ ሲሆን፥የትምህርት ደረጃ 2ኛ ደረጃ ካጠናቀቁ በኋላ የነርስንግ ድፕሎማ አግኝተዋል። በአሁኑ ጊዜ በግል ንግድ ሥራ ተሰማርተዉ በደቡብ አፍሪካ ይገኛሉ።

ሊሬ አባተ፣ የአባተ መኒሶ ማህበር በጎ አድራጎት ቦርድ አባል ሂሳብ ሰራተኛ የማህበሩን ሂሳብ በበቂ ሰነድ በተደገፈ መልኩ የገቢና ወጪ ሂሳብ ሰርተዉ  የሂሳብ ሪፖርት የሚያአቅርቡ ሲሆን፥ የትምህርት ደረጃ በአካዉንትንግ የመጀመሪያ ዲግሪ ከኢትዮጵያ አድቬንቲስት ኮሌጅ እና  ከአምቦ ዩኒቨርሲቲ በኬሚስትሪና ሂሳብ የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝተዉ በአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ት/ ቤት በማስተማር ላይ ይገኛሉ።

**ሆመቾ ሆስፒታል ደርሶ መልስ ትራንስፖርት፥ በገጠር ቀበሌያት ሆስፒታል ለመሄድ ትራንስፖርት አጥተዉ የሚቸገሩትን መርዳት**

**ዓባሪ**

መተዳደሪያ ደንብ
የድጋፍ ደብዳቤ
የቦርድ አባላት ፎቶ
የቦርድ አባላት ትምህርት ማስረጃ
የቦርድ አባላት ሥነ ምግባር
የአባላት ፊርማ